**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**
**Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)**

ሚያዚያ 26 ቀን 2006 ዓ.ም.
May 3, 2014

# ነፃ ፕሬስ፤ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር አንድም ሶስትም ናቸው !

በባለሙያዎቹ አገላለፅ መሰረት ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተከበሩበትና መልካም አስተዳደር በተመሰረቱበት ሕብረተሰብ ውስጥ ነፃ ፕሬስ በዋናነት የመንግሥትን አሰራር ለሕዝብ፤ በሕዝቡ ውስጥ የሚንሸራሸሩትን ፍላጎቶች፤ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ደግሞ በሥልጣን ላይ ለሚገኘው አካላትና ተቋማት በማስተላለፍ በሁለቱ ክፍሎች መካከል ድልድይ በመሆን የሚያገለግል እንደሆነ ነው። በዚህም ሁኔታ ነፃ ፕሬስ መንግሥትንና ሕዝብን የማገናኘት፡ አስተያየትንና ብሶትን የመግለጫና የጋራ መፍትሄ መቀየሻ ሚና ይኖረዋል ተብሎ አፅንዖት በተሞላበት አኳኋን በርካታ ተመክሮን ባገኙ ሙያተኞች ይገለፃል። ይህ ብቻ አይደለም።

ነፃ ፕሬስ

- ለተስታፎ ፍላጎትና ችሎታ ያላቸው ዜጎችን እውቀታቸውን ያሳድጋል፤
- ሕዝብ ሊወያይበት የሚገባቸውን ፖለቲካዊ ርዕሶች ይቀርፃል፤
- ወሳኝ በሆኑ የፖለቲካ ርዕሶች ላይ የራሱን ትንታኔ በማቅረብ ለውይይት ያቀርባል፤
- በዜጎች መካከል የሃሳብና የአስተያየቶች መለዋወጥ የሚያስችል መድረክ ያዘጋጃል፤
- የፖለቲካና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ እንዲረጋጋ የበኩሉን አስተዋፅዖ ያበርክታል፤
- የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች የሚያሳልፉትን ውሳኔ የሚደነግጉትን ሕግና ደንብ ተከታትሎ ለሕዝብ በማቅረብ ይተቻል፤ ያስተቻል፤
- ፖለቲከኞች ስለ ራሳቸውም ሆነ ተግባራቸው የሚያሳድሩት ተፅዕኖም ሆነ ከሕዝብ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት በጥሞና እንዲያስቡ በማድረግ መልካም ሃሳቦች እንዲጎለብቱ፤ መታረም ያለባቸው ደግሞ እንዲታረሙ መድረኩን ያመቻቻል።
- በመንግሥት አሰራር ሂደት ውስጥ የተፈጠሩ፤ ወይንም ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉድለቶችና ስህተቶችን እንዲሁም ማናቸውን የተለያዩ ክፍተቶችን በበቂ ጥናትና መረጃዎች ላይ በመመስረት ነቅሶ በማውጣትና በማጋለጥ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

ታዲያ ባለመታደል ሆኖ ኃይልን መከታ በማድረግ በሕዝብ ጫንቃ ላይ የተቆናጠጠው የወያኔ ጎሰኝና አምባገነን አገዛዝ በመላው አለም ተቀባይነት ያገኙ የፕሬስ ሕጎችን በሕገ አገዛዙ አካትቼያለሁ እያለ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም በተግባር ግን ይህንኑ ተፃርሮ ይገኛል። በተለያዩ ጊዜያት በነፃ ፕሬሱና አባላቱ ላይ እያደረሰ ያለው በደልና እንግልት የዚሁ ውጤቶች መሆናቸው ሊካድ የማይችል ነው። ይህም የሚያመለክተው በሕገ አገዛዙ ሰፍረው ያሉትና ዋስትና አግኝተዋል እያለ የሚመፃደቅባቸውን የሕግ አንቀጾች እንኳ ዜጎች አግባብነት አለው ባሉበት ሁናቴ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብታቸውን ተግባራዊ እንዳያደርጉ በአደባባይ እየጣሰ ይገኛል። በራሱ ውሳኔና ተግባራት እምነት የለውምናም ሊቀርቡበት የሚችሉትን ትችቶች እንደ ጦር በመፍራት ጋዜጦችን፤ መፅሄቶችን ዘግቷል፤ አግዷል፡፡ የተለያዩ ድረ ገፆችን አፍኗል፤ የኢንተርኔት መገናኛዎችን መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን መጥለፍና ማገድ፤ የሬዲዮ ስርጭቶች በባዕዳን እየተረዳ እንዳይሰሙ አድርጓል። የነፃ ፕሬስ አባላትን በተደጋጋሚ ለእስርና ለእንግልት ብቻ ሳይሆን ደብዛቸው የጠፋ፡ ለስደትና በአሰቃቂ ሁናቴ ለሞት በመዳረግ የሕዝብን ማናቸውንም መረጃ በነፃነት የማግኘት መብታቸውን ክፉኛ እየደፈጠጠ ይገኛል። በዚህም በርካታ የፕሬስ ውጤቶች ከመድረኩ ላይመለሱ ተገለዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በኢትዮጵያ የነፃ ፕሬስ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የሕግ የበላይነት አለ ተብሎ የሚለፈፈው የማስመሰያ ፕሮፓጋንዳ ከመሆን የሚያልፍ አለመሆኑን ጭምር ነው።



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

በቅርቡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ጋዜጠኞችና ጦማሪያንን ዘብጢያ ማውረዱ ብቻ ሳይሆን ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ቀርቦ የማስረጃ ሁለመና ተአሚነት ከመረጋገጡ በፊት ከወዲሁ በአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች እየተሰነዘሩ ያሉ ውንጀላዎች ከሳሽ፤ ዳኛና ፈራጅ በመሆናቸው የሕግ የበላይነት የሌለና ፍትህ ደብዛዋ የጠፋ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

የፕሬስ ነፃነት አዋጅ ተብዮው በ1985 ዓ.ም. ከታወጀ ወዲህ ያሉት አመታት እንደሚያረጋግጡት አገዛዙ ራሱ ያወጀውን ሕግ ለማክበር ምንም አይነት ቅንነትና ፍላጎት የሌለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለግሉ ፕሬስ ያለው አመለካከት ድርጊቶቹ እንደሚመሰክሩበት ድጋፍ ሰጪ ሳይሆን በአፍራሽነት የተሰማራ አገዛዝ እንደሆነ ነው። በራሱ አምሳያ የቀረፃቸውንና በሕዝብ ኃብት የሚያስተዳድራቸው የዜና ተቋማትን በልማታዊ ጋዜጠኝነት ሥም እንዳሻ የሚያሽከረክራቸው በመሆኑ ለፕሬስ ነፃነት ያለውን ጠላትነት በእጅጉ የሚገልፁት ናቸው። ይህ ብቻ አይደለም። የሚደርስባቸውን የተለያዩ እንግልቶች እየተቋቋሙ ቢሆንም ለሕትመት የሚያበቋቸው ጋዜጦቻቸው በጊዜው ባለመውጣት የሚደርስባቸው መንገላታት፤ ከውጭ በሚገቡ የወረቀት ምርት ላይ የተጣለው ታክስ እነሱም ሆኑ ጋዜጣዎቻቸውን ለመግዛት አቅም ያለው ጥቂት ዜጋ እንኳን የሚደርስባቸው መጎሳቆልና ቁጥራቸው በእጅጉ እየቀነሰ መምጣቱም አድማጭ ያጣ የእሮሮ ድምጽ እያቀረቡ መሆናቸው የሚደበቅ አልሆነም። በዚሁ ከቀጠለም ለበርካታዎቹ ደርሶ የነበረው ብዕራቸው ሊዶለድም፤ አፋቸው በልጓም ሊዘጋ፤ እጃቸውና እግራቸው በካቴና ሊታሰርና ወደማይቀርላቸው የሕሊና እስር ቤት ለመታሰር ቀናቸውን እየተጠባበቁ ይገኛሉ። እንደ ሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ሁሉ የነፃ ፕሬስ አባላትም የነፃነት አየር ለመተንፈስ አልተቻላቸውም።

በዛሬው እለት ሚያዚያ 25 ቀን 2006 ዓ.ም. (ሜይ 3 ቀን 2014) አለም አቀፍ የፕሬስ ቀንን ስናከብርና በሀገራችን የፕሬስ ተቋማትና የአባላቱን ሁናቴ በሕሊናችን ስናሰላስል ለአገዛዙና ለደጋፊዎቹ ካልሆነ በስተቀር የሚዘገንንና የሚሰቀጥጥ ብቻ ሳይሆን እጅግ ቀፋፊ የሆነ የፖለቲካ ድባብ ባንዣበበት ምህዳር ለመንቀሳቀስ የተገደዱበት መሆናቸውን እንመለከታለን። የፕሬስ ነጻነት ደባው ተፈልጎ የሚገኝ አይደለም። አባላቱ የደህንነት ዋስትና ስለሌላቸው በስጋት ድባብ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። የመናገርና ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ያለገደብ ስለማይከበር ነፃ ፕሬስ ሊኖር አልቻለም። ጋዜጠኞች ሳይወዱ በግዴታ ራሳቸውን በራሳቸው ሳንሱር እንዲያደርጉ ይገደዳሉ። አገዛዙን የሚያጋልጡ ቀርቶ የሚነቅፉ ሲቀርቡ በአሸባሪነት ይከሰሳሉ። በርግጥም ኢትዮጵያዊያን ሀገር ወዳድና ለሕዝባቸው ቀናኢ የሆኑ ዜጎች ከነፃ ፕሬስ አባላት ጋር ይህንን ቀን ሲያከብሩ አገዛዙ እንደሚያደርገው ለመመፃደቂያ ትርጉም የለሽ መግለጫዎችን በማውጣትና ሴሚናር በማዘጋጀት የጨቀየ ሥእላዊ ገፅታቸውን በፕሮፓጋንዳ ለማጠብ ሲል በወረቀት ያሰፈራቸውን ነገር ግን ደግሞ የተጻፉበትን ወረቀት ያህል እንኳ ክብደት የሌላቸውን አንቀፆች እንደገደል ማሚቶ ደጋግሞ በመጥቀስ አይደለም።

በሀገራችን ነፃ ፕሬስ ሊከበር ያልቻለው የአገዛዙ አፈቀላጤዎች እንደሚነዙት ሙያውንና የሥነ ምግባር ደንቡን በሚገባ ተረድተው ሊሰሩ የሚፈልጉና የሚችሉ ጋዜጠኞች ጠፍተው ወይንም ደግሞ ሕብረተሰባችን ስለ ነፃ ፕሬስ ሙያ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ ሆኖ መረጃን ሙያዊ ሥነምግባር ተላብሰው ዜና ከሚያቀርቡ ጋዜጠኞች ይልቅ ለፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ አይነት ውጤቶች ትኩረት የሚሰጥ ሆኖም አይደለም። ወይንም ደግሞ ሕዝባችን ከተለያዩ የዜና ተቋማት የሚሰጡ ዜናዎችን አይቶም ሆነ ተመልክቶ እውነቱን ከውሸቱ፤ ተራ ፕሮፓጋንዳና ዘለፋን ሥነ ምግባር በተሞላበት የተገኘ መረጃን ለይቶ የራሱን የሕሊና ፍርድ ለመስጠት የማመዛዘን ችሎታ አንሶት እንዳይደለ በተደጋጋሚ ብስለቱን ያንፀባረቀ ነውና በዚህ ሊታማ የሚችልበት ምንም አይነት መረጃ የለም።
ይልቁንስ በኛ እምነት ለምሳሌ ሙስናን በተጨባጭ እንዳያጋልጥ፤ ለመልካም አስተዳደር መመስረት እንቅፋት የሆኑትን እንዳይታገል፤ ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መበት መከበር እንቅፋት የሚሆኑ ኃይሎችን ግልምጫና ጫና ሳይበግረው ዜናዎችንና ትችቶችን በማቅረብ እንዳያጋልጥ፤ በሕግ የበላይነት ላይ የተመረኮዘ መልካም አስተዳደር በሚኖርባት ሀገሩ እንዲመሰረት እንደ ሌሎቹ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዳያበረክት በወያኔ አገዛዝ የተመሰረተው የፖለቲካ ሥርአት እንቅፋት ሊሆንበት በመቻሉ ነው።



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

ጋዜጠኞች በሀገሪቷ መፃኢ እድል መሃል ሰፋሪ የሆኑ፤ የራሳቸው ራዕይና አስተያየት የሌላቸው አይደሉም። አቅማቸውንና እንደማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ያለባቸውን ድክመት በሚገባ የሚገነዘቡ ለመሆናቸው ያለምንም የመንግሥት ጣላቃገብንት የሕዝብ አንደበትና ጆሮ ሆነው በሙያቸው ለማገልገል እድሉን ለጥቂት ወራት ባገኙበት ወቅት ሳይቀር ከበቂም በበቂ አስመስክረዋል። ሲበረታባቸው እንጂ ከማንኛውም አቅጣጫ የተቃጣባቸውን ጫና ተቋቁመው ነፃነታቸውን ለማስጠበቅ የአቅማቸውን የጣሩ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነውና የምንረሳው አይሆንም። የገንዘብ አቅማቸው ደካማና ካለው አገዛዝ ምንም አይነት ድጋፍ እንደማያገኙ ባወቁበት ጊዜም ቢሆን በራሳቸው ጥረት አገልግሎታቸውን ለሕዝብ ለማቅረብ ጣሩ እንጂ ከተጨባጩ ሁኔታ የወጣ ልዩ ተአምር ከማንም የጠበቁ አልነበሩም። ያሉባቸውን ጉድለቶች በሚመለከትም አገዛዙ በሚያደርጋባቸው የተለያዩ እንግልቶችና በደሎች የተነሳ ከመድረኩ ለመገለል እስካስገደዳቸው ድረስ እርስ በርሳቸው በጋራ መፍትሄ ለማፈላለግ ጣሩ እንጂ ከማንም ጫማ ሥር ለመነጠፍ አልከጀላቸውም።

በኛ እምነት ነፃ ፕሬስ፤ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር አንድም ሶስትም በመሆናቸው ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም። ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች በታፈኑበት ነፃ ፕሬስ ሊኖር አይችልም። ነፃ ፕሬስ በሌለበት ሁናቴ ደግሞ መልካም አስተዳደርም ሆነ ፍትህና የሕግ የበላይነት ሊኖሩ አይችሉም። ስለሆነም ነፃ ፕሬስ በኢትዮጵያ በአባላቱ ቆራጥ ትግል፤ በሀገር ወዳዱ ከፍተኛ ድጋፍና ተጋድሎ የወያኔን አገዛዝ አስወግዶ በነሱ መቃብር ላይ የሚመሰረት እንጂ የአሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ መሆኑ ተረስቶ ራሱኑ ወያኔን በመለማመጥ፤ የማሳሰቢያና የአቤቱታ መልዕክት ለሱ በማስተላለፍ፤ የሚገኝ ከቶ ሊሆን አይችልም።

በዛሬው እለት አለም አቀፍ የነፃ ፕሬስ ቀንን ስናከብር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው መልዕክት የወያኔን አገዛዝ ከሥልጣን አስወግዶ ዴሞክራሲ ሥርአት መገንባት የሚለው ብቻ ነው። ይህ አላማ በጋራና በቆራጥ ትግል ስኬታማ ሲሆን ያረረው አንጀታችን የቆሰለው ሕሊናችን ይታበሳል። የነፃነት አየር አብረን እንተነፍሳለን። ያኔ በትግል ላጣናቸው የነፃው ፕሬስ አባላት በልባችን ውስጥ ለገነባንላቸው የማስታወሻ ኃውልታቸው እቅፍ አበባ በያመቱ እያስቀመጥን ምንጊዜም ላንረሳቸው የገባነውን ቃልኪዳን እናድሳለን።

ነፃ ፕሬስ ለመፃዒቷ ኢትዮጵያ!




**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**